# የኢትዮጵያ ፖለቲካ የአንድ ሰው አገዛዝ እንዳይሆን የሠጉ አሉ

**ኢሕአዴግ ስምንተኛ መደበኛ ጉባዔውን አጠናቀቀ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስና ወጣት መንግሥት ይመሠርታሉ እየተባለ ነው፡፡**

በ ፒተር ሃይንላይን / ሰሎሞን አባተ | አዲስ አበባ17 September, 2010

የኢትዮጵያው ገዥ ፓርቲ በሣምንቱ ውስጥ ስምንተኛ ጉባዔውን አካሂዷል፡፡ጉባዔው ፓርቲውን በወጣት አመራር ለመተካት በሚቻልበትና ተስፋ በጣለበትየአምስት ዓመት የምጣኔ ኃብት ዕቅድ ላይ ለመነጋገር ነው አጀንዳ የያዘው፡፡አዲሱ የፓርቲው አደረጃጀት ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊንሥልጣን የሚያጠናክር እንደሚሆን ተንታኞች ይናገራሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊግንባር (ኢሕአዴግ) ስምንተኛ መደበኛ ጉባዔን ያስጀመሩት ሃገሪቱ የኖረችበትንየውጭ ምግብ ዕርዳታ ጥገኝነት በመጭዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ለመስበር ቃል በመግባት ነበር፡፡

በርግጥ ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተስፋ ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ካሣለፈችው ሕይወቷ ጋር ፊት ለፊትየሚጣረስ ነው፡፡ የተራዘመው ረሃብ አሁንም ቢሆን ከስድስት ኢትዮጵያዊያን አንዱን ረሃብተኛ ያደረገበት ጊዜ ነው፡፡ዩናይትድ ስቴትስ ብቻዋን እንኳ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ከግማሽ ቢልዮን ዶላር በላይ ግምት ያላቸውየምግብና ሸቀጣ ሸቀጥ አቅርቦቶች ያስገባችበት ዓመት ነው ያለፈው፡፡ ይህ በቀድሞው ምንዛሪ እንኳ ሲሰላ ወደ ሰባትቢልዮን የኢትዮጵያ ብር የሚጠጋ ገንዘብ መሆኑ ነው፡፡

ይህ የአዳማ ጉባዔ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የሽግግር ዕቅድ በይፋ የሚገለጥበት፣ የአቶ መለስ ዜናዊ የኢሕአዴግመሪነት፣ "የአንድ ፓርቲ የበላይነት" እያሉ በሚጠሯት ሃገር ላይም መንበረ ሥልጣኑን እንደጨበጡ እንደሚቀጥሉብድጋሚ የሚረጋገጥበት ይሆናል ተብሎ ነው የሚጠበቅ፡፡

ይህ ስብሰባ የተጠራው ፓርቲው ዋና የሚባል ለውጥ በራሱ ላይ እያካሄደ መሆኑ በሚነገርበት ወቅትም ነው፡፡ አቶ ስዩምመስፍንን የመሣሰሉትን ጨምሮ አንጋፋ ናቸው የሚባሉ የግንባሩ ሰዎች ብርቱ ናቸው ከሚባሉቱ የአካባቢ የፖለቲካቢሮዎች ሁሉ መውጣታቸው ተሰምቷል፡፡ አቶ መለስ በሚቀጥለው ወር ያደርጉታል በተባለ ሹም ሽር አዳዲስ ፊቶችንበመንግሥታቸው ውስጥ ለማስተናገድ መዘጋጀታቸውንም ሲጠቋቁሙ ተደምጠዋል፡፡

ይሁን እንጂ ያ ብወዛ ምን እንደሚያመጣ፣ እነማን እንደሚወጡ፣ እነማን እንደሚወድቁ ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም-

አሁን ላለው ጊዜ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አቶ መለስ የቀድሞ የትግራይ ሽምቅ ንቅናቄ ጓዶቻቸውን ዘወር አድርገውበአዳዲስና ወጣት የፓርቲ ታማኞች ቢተኳቸው የሚከተለው ነገር ቢኖር እንዲሁም የሙጥኝ ብለው የጨበጡትንሥልጣን የሚያጠናክርላቸው እንደሚሆን የአፍሪካ ቀንዱ የፖለቲካ ተንታኝ መድኅኔ ታደሰ ሲናገሩ

"አዲሶቹ የምንላቸው ሰዎች መምጣት ከለውጥ ወይም ሂደቱን ከመቀየር ይልቅ ባለበት ሁኔታ የሚያጠናክረው ብቻ ነውየሚሆነው፡፡ ምክንያቱም መለስ ሃሣቦቻቸውን የሚያቀርቡት ለድሮ ጓዶቻቸው ሳይሆን ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎችለተሰባሰቡ፣ አንዳችም የትግልም ይሁን በራሣቸው የያዙት የፖለቲካ ማንነት ለሌላቸው አዳዲሶቹ ሰዎች ነው፡፡ በመሆኑምይህ እርምጃ የግል ተፅዕኗቸውን የሚያጠናክርላቸው ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እንደኀሉየሚቀጥሉት የርሣቸው የግል ሃሣቦች፣ የርሣቸው ተክለማንነት ይሆናሉ፡፡" ብለዋል፡፡

ይህ ሥልጣንን የመሰባሰብና የማጠናከር አዝማሚያ ሃገሪቱን ወደ አንድ ግለሰብ አገዛዝ ሥርዓት እንዳይወስዳት ይሠጋሉመድኅኔ፡፡ እንዲህ አሉ፡-

"በቅርብ ጊዜው የኢትዮጵያ ፖለቲካ አሣዛኝ የሆነው ጉዳይ መንግሥቱም፣ ገዥ ፓርቲውም፣ ሕግ አውጭውም ሁሉምአንድና እርሱው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ አንድ ብርቱ የሚባል ሰው መኖር የሚያሣየው እንዲያው እንደወትሮውዓይነት የሃገርን፣ የገዥ ፓርቲንና የመንግሥትን መጣጣም አይደለም፡፡ ባለፉት ዓመታት ጉዞ ውስጥ የጋራ አመራርየሚባል ነገር ተመናምኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርቲያቸው ውስጥ ብቻ ሣይሆን ዛሬ በደረስንበት ሁኔታ በሃገሪቱናበመንግሥቱ መዋቅሮች ውስጥ በሚከናወነው ሥራ ሁሉ ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ሆነዋል፡፡"

ኢሕአዴግ በለውጥ እንደገና ለመደራጀት የያዘው አቋም "ደፋር እርምጃ" ነው የሚሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲውየፖለቲካ ሣይንቲስት ሰሎሞን መብሬም ቢሆኑ ሥጋት አላቸው፡፡ በፓርቲና በመንግሥት መካከል ግልፅ የልዩነት መሥመርያለመኖሩ ጉዳይ ለሙስና መቀፍቀፍ ምቹ ሁኔታዎችን ሊፈጥር እንደሚችል ይናገራሉ፡፡

"በመንግሥትና እንደ ፖለቲካ ድርጅት ደግሞ በኢሕአዴግ መካከል መኖር ይገባው የነበረው ልዩነት በውል እንዳይታወቅየመደብዘዙ ጉዳይ የተወሰኑ የመንግሥት አሠራሮች እና በታች ደረጃ ያሉ አባላቱ ለግል መግነኛ በመሣሪያነትእንዲጠቀሙበት አስችሏል፡፡ ይህም የተጠያቂነትና የሕግ የበላይነት መርሆች በከባዱ ተጨፈላልቀው ለአስተዳደሩመበላሸት ዋና በሚባል ሁኔታ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡" ብለዋል ሰሎሞን መብሬ፡፡